የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአራተኛ ዓመት ቁጥር ፶፮
አዲስ አበባ ነሐሴ ፭ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No 56.
ADDIS ABABA 11th August, 2008

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፱/፪ሺህ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥ ትና በህንድ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመን ትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገውን ስምም ነት ማፅደቂያ አዋጅ … ገጽ ፬ሺ፩፻፺፰

CONTENTS

**Proclamation No. 599/2008**

Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of India on the Promotion and Protection of Investment Ratification Proclamation Page 4198

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፱/፪ሺ

## ከህንድ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በህንድ ሪፐብሊክ መንግሥት መካ ከል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስ ጠት ግንቦት ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ስምምነት በአዲስ አበባ ላይ የተፈረመ በመሆኑ፣

ስምምነቱ ሥራ ላይ የሚውለው በተዋዋዮቹ ሀገ ሮች ህጎች መሠረት መጽደቁን የሚያረጋግጡ ሰነዶች በዲፕሎማቲክ አካላት አማካኝነት ልውውጥ ከተደረገ በኋላ እንደሆነ በስምምነቱ ስለተገለጸ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክ ራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፯ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION NO. 599/2008.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT ON THE PROMOTION AND PROTECTION OF INVESTMENT WITH THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF INDIA

**WHEREAS,** the Agreement on the Promotion and Protection of Investment between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of India was signed in Addis Ababa on June 5,2007;

**WHEREAS,** it is stipulated in the Agreement that it shall enter into force on the date of exchange of instruments of ratification through diplomatic channel of the parties;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the Agreement at its session held on the 4th day of July, 2008;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Sub-Article (1) and (12) of Article 55 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

፩. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በህንድ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተፈረመው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፱/፪ሺ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. <u>**ስምምነቱ ስለመጽደቁ**</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በህንድ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት በአዲስ አበባ ከተማ ግንቦት ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም የተፈረመው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

፫. <u>**የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ኃላፊነት**</u>

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. <u>**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፭ ቀን ፪ሺ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

1. <u>**Short Title**</u>

This Proclamation may be cited as the "Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of India on the Promotion and Protection of Investment Ratification Proclamation No. 599/2008".

2. <u>**Ratification of the Agreement**</u>

The Investment Promotion and Protection Agreement signed in Addis Ababa on June 5, 2007 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of India is hereby ratified;

3. <u>**Power of the Ethiopian Investment Agency**</u>

The Ethiopian Investment Agency is hereby empowered to implement this Agreement.

4. <u>**Effective Date**</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 11th day of August, 2008**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**